# መጽሔተ ተልእኮ
# ዘማኅበረ ቅዱሳን





ግንቦት ፳፻፲፯ ዓ.ም

# ማውጫ


መልእክት ........................................................ 1
ቅኝት ........................................................ 3
ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን ........................................ 7
ሰማዕትነት ................................................ 17
ብሒለ አበው ............................................ 19
ኪነ ጥበብ ................................................ 20


"መጽሔተ ተልእኮ ዘማኅበረ ቅዱሳን" የሚለው ሐረግ ከግእዝ ቋንቋ የተገኘ ነው። "መጽሔት" ጸሐወ /ጸሐየ/ በራ፤ ጠራ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሆኖ መስታዎት ማለት ነው። "ተልእኮ" የሚለው ቦዝ ቃል "ለአከ፤ ላከ ሰደደ" ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን በትርጉም አገልግሎት ማለት ነው። ይህ መጽሔት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በቅዱስ ሲኖዶስ በጸደቀለት መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በየደረጃው ባሉት የአገልግሎት መዋቅሮች የሚያከናውናቸውን ተግባራት የሚያሰውቅበት በመሆኑ "መጽሔተ ተልእኮ ዘማኅበረ ቅዱሳን" የሚለውን ስያሜ አግኝቷል።


አዘጋጅ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ማስተባበሪያ

ግንቦት ፳፻፲፫ ዓ.ም

# “ግቢ ጉባኤ ላይ መሥራት ለነገዋ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ተጸራሽ ግብር ነው”

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ኦርቶዶክውያን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመማር ራሳችንን ከክሕደት መጠበቅ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንንና የሀገርን ታሪክ አውቀን በቅንነት በማገልገል ለሌሎችም አርአያ መሆን ይገባናል ብለው የወሰኑ ኦርቶዶክሳውን በግቢ ጉባኤ ተሰብስበው መማር ከጀመሩ አራት ዐሥርት ዓመታትን ሊያስቆጥር ዋዜማ ላይ ነው:: የእነዚህ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች መሰባሰብም ማኅበረ ቅዱሳንን ሊያስገኝ ችሏል::ማኅበረ ቅዱሳንም ግቢ ጉባኤ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራው ግቢ ጉባኤ ለሀገርና ለቤተክርስቲያን ብቁ ትውልድ መፍጠሪያ ተቋም ስለሆነ ነው::

የማኅበረ ቅዱሳን አመሠራረት እና የአገልግሎት ጅማሮ ኩነት የተገኘው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚማሩ ተማሪዎች የቤተ ክርስቲያናቸው ትምህርት ለትውልድ ተደራሽ ካለመሆኑ የተነሳ ይህን ክፍተት ለመሙላት በተደረገ ጉዞ ነው:: ለዚህም ነው ማኅበረ ቅዱሳን ሲታወስ ግቢ ጉባኤ፣ ግቢ ጉባኤ ሲታወስ ማኅበረ ቅዱሳን በኅብረት የሚወሳው::

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከራሷ አልፎ ለዓለም ሕዝብ የሚተርፍ ዘመን ተሻጋሪ አሻራዎችን ስታስቀምጥ፣ ታሪክን ስትሠራ በመኖሯ የዘመናችን ትውልድ በቀደመ ታሪኩ እንዲኮራና ሀገር ወዳድ እንዲሆን አስችሏል:: ሀገርን በመገንባት ረገድም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አሻራዋ ሁለንተናዊ መሆኑ ይታወቃል:: ይህም የኢትዮጵያ ታሪክ የቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያንም ታሪክ የኢትዮጵያ እየሆነ በተመጋጋቢነት የኖረ ትስስሩ በእጅጉ የተቆራኘ አኗኗር ነው:: ከዚህ በተለየ የሀገራቸውን ታሪክ ጠንቅቀው ያላወቁና ምዕራባውያን የጫኑባቸውን ሸክም ተሸክመው አላዋቂነታቸውን የሚያስተጋቡ የዚህ ዘመን ስሑታን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለሀገር የከፈለችውንና ያበረከተችውን አይተኬ ሚና በመዘንጋት”ባጎረስሁ ተነከስሁ”እንዲሉ ለሀገር ኋላቀርነትና ድህነት ምክንያት ያደርጓታል::

# መልእክት

የማኅበረ ቅዱሳን መመሥረት እነዚህ አካላት የያዙትን እኩይ ዓላማ ከንቱ የሚያደርግባቸው መሆኑን የተረዱ የምዕራባውያን ጉዳይ አስፈጻሚ ተሐድሶዎችና መናፍቃን ማኅበረ ቅዱሳንን ስሙን ለማጥፋትና ለማጠልሸት ቢዳዱም የተቋቋመው በፈቃደ እግዚአብሔር ነውና ክፉ ተግባራቸውን ማስፈጸም አልተቻላቸውም።

ለዚህም ጉዳያቸው በየጊዜው መንግሥት ጋር በመወዳጀት ማኅበሩን ከቤተ ክርስቲያን መዋቅር ለማስወጣት እንቅልፍ አጥተው የሚደክሙ ትውልዱ የሀገርና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ከተረዳ የያዙት እኩይ ድርጊት ከንቱ እንደሚቀርባቸው በመረዳታቸው ነው።

ሃይማኖት ሳይኖራቸው ጽኑ ሃይማኖተኛ መስለው አገራችንን ለባዕድ አሳልፈው ለመስጠት የተቀበሉትን ተልዕኮ ከንቱ ሲያደርጉባቸው የኖሩት በግቢ ጉባኤያት ተሰባስበው በመማር ለቤተ ክርስቲያን ጠበቃ የሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን የወለዳቸው ልጆች ናቸው። አገራችንም ይሁን ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ማኅበረ ቅዱሳን ያሉትን በወጣቱ ትውልድ ላይ የሚሠሩ ማኅበራትን ማጠናከርና ቁጥራቸውንም ማብዛት ቢቻል እንደምን ያለ መታደል ነበር ።

ሃይማኖተኛ መሆንን እንደ ኋላቀር እና ሞኝነት ተደርጎ በሚቆጠርበት ዘመን ኦርቶዶክሳውያን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ግቢ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም በቅዱስ ገብርኤል ስም በ፰ ወጣት ወንድ ተማሪዎች የተጀመረው ግቢ ጉባኤ በዘመናችን ቁጥሩ ከአራት መቶ ኀምሳ በላይ ደርሷል። ማኅበረ ቅዱሳን የሚከውነው በእነዚህ ጉባኤያት የተሰበሰቡ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ትውልድ በሚገባ በማነጽ ቤተ ክርስቲያኑንም ሆነ አገሩን እንዲያገለግል ብቁ ማድረግ ነው። ያለ አድሎና ሙስና ሥራ በማይሠራበት በዚህ ዘመን ትውልድን ሁሉ እኩል የሚያገለግል፣ አድሎን የሚጸየፍ፣ ሥራ ወዳድና ሰው አክባሪ ትውልድ ከማፍራት በላይስ ምን የህልውና ጉዳይ ይኖራል?ለዚህም ነው ማኅበረ ቅዱሳን ዕለት ዕለት ሁነኛ ጉዳይ አድርጎ የሚሠራው፡ ለዚህም በጎ ግብር የግቢ ጉባኤ ጤናማ አኗኗርና ህልውና የጎላ ድርሻ አለው።

# በሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ዋና ክፍል

በዛሬው ቆይታችን በማኅበረ ቅዱሳን ዋና ማእከል ሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ ውስጥ ከሚገኘው ቅድመ ግቢ ጉባኤ ዋና ክፍል ተብሎ ከሚጠራ የአገልግሎት ዋና ክፍል ጋር ስለ ክፍሉ አመሠራረትና ፋይዳውን በተመለከተ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ዋና ክፍል ከመመሥረቱ በፊት ሐሳቡን ካመነጩትና ሐሳቡም ተቀባይነት አግኝቶ ክፍሉ እንዲመሠረት ካደረጉት አባላት መካከል እንግዳ አድርገን ጥያቄዎችን እንዲመልሱልን ጋብዘናቸዋል። እንግዳችን ወ/ሮ ዓይናለም ታየ ይባላሉ፤ በማኅበረ ቅዱሳን በከፍተኛ አመራርነት እያገለገሉ የሚገኙ ሲሆን ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንድትከታተሉ እንጋብዛለን፤ መልካም ቆይታ!

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ቅድመ ግቢ ጉባኤ ማለት ምን ማለት ነው? አመሠራረቱ ምን ይመስላል? ትኩረቱስ ምን ላይ ነው?

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡-** ማኅበረ ቅዱሳን ከተቋቋመበት አንዱ ወደ ከፍተኛ ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች በተሰማሩበት ሙያም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማግኘት የሚገባቸውን ትምህርትና አገልግሎት አግኝተው ብቃት ያለው ዜጋ እንዲሆኑ በማድረግ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት ነው። ነገር ግን ተማሪዎች ግቢ ጉባኤ ከመግባታቸው በፊት በተለያዩ ዘመን አመጣሽ ጉዳዮች ተጠምደው ስለሚመጡ ቀደም ባለ ዕድሜያቸው አግኝቶ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመግባታቸው በፊት ማዘጋጀት እና ማስተማር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ይህንንም ለመተግበር የማኅበሩ አመራር ቅድመ ግቢ ጉባኤ በሚል አገልግሎቱ እንዲጀመር ወሰነ። ቅድመ ግቢ ጉባኤ ማለት ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ (ግቢ) ከመግባታቸው በፊት በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቆይታቸው ወቅት ከትምህርታቸው ጎን ለጎን በሰንበት ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርት እና የቀለም ትምህርታቸውን ማጠናከሪያ የሚማሩበት ለጥሩ ውጤትና በመልካም ሥነ ምግባር የሚቀረጹበት አገልግሎት ነው። ትኩረቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታዊ ትምህርት እና በኢትዮጵያ የሚሰጠው የቀለም ትምህርት ነው።

## ቅኝት

**መጽሔተ ተልእኮ:-** የቅድመ ግቢ ጉባኤ ትምህርት እንዴት ተጀመረ?

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ:-** ትምህርቱ የተጀመረው የማኅበሩ ሥራ አመራር በግቢ ጉባኤ የሚሰጠውን ትምህርት ለመስጠት ተማሪዎቹ ወደ ግቢ ከመግባታቸው በፊት ቀድሞ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን በተለያየ መልኩ በሚቀርቡ ጥናቶች ስለተረዱ፣ ለምሳሌ የሕይወት ቆይታቸው የተበላሸና በዓለማዊ ተጽእኖ ውስጥ ከወደቀ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሲገቡ በግቢ ጉባኤ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ቀርበው ለመማር ፍላጎት አይኖራቸውም እንዲሁም ትምህርቱን ለመቀበልም ይቸገራሉ የተወሰኑት ተማሪዎች የሚያገኟቸው እና የሚጠቀሙባቸው የአስኳላ ትምህርት መጻሕፍቶች፣ አጋዥ መጻሕፍቶች እና የቴክኖሎጂ ውጤቶች በዓለማዊው ተጽእኖ ሥር የወደቁና የተበላሹ እሳቤዎች ስለሆኑ፣ ሱስ፣ ግብረ ሰዶም እና ሌሎችም መጥፎ ምግባሮችን ሊለምዱ ስለሚችሉ ቀድሞውኑ ወደዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ እንዳይወድቁ እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ቀድመው ለምደው ለሚመጡ ተማሪዎች በግቢ ጉባኤ የሚሰጠውን ትምህርት ለመማር ፍላጎት አይኖራቸውም፤ ትምህርቱን ለመማር አያነሳሳቸውም፡፡

በመሆኑም ይህ ጉዳይ ቅድመ ግቢ ጉባኤን ለመመሥረት እንደ ገፊ ምክንያት ሆኖ ተማሪዎች ግቢ ከመግባታቸው በፊት ሊሠራባቸው እንደሚገባ ስለታመነበት ቅድመ ግቢ ጉባኤ እንዲመሠረት ኮሚቴ ተቋቁሞ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ጥናት ተደርጓል፡፡ በጥናቱ መሠረትም አብዛኛው ወጣት ግቢ ከመግባቱ በፊት እየገጠመው ያለው ችግር በጥናት እየተለየ በመምጣቱና ችግሩ ስለታወቀ በቀጣይ ወደ ግቢ ከሚገቡ ተማሪዎች 50% (ሃምሳ ከመቶ) የሚሆነው ወጣት ወደ ቤተ ክርስቲያን ላይመጣ የሚችልበት አዝማሚያ ስለታየ፣ ወጣቱን በሉላዊነት ወይም በግሎባላዊነት ከሚመጣ ዘመናዊነት መሰል መጥፎ ምግባሮች ለማዳንና ትውልዱን ከክፉ ልምዶች ለመታደግ ትምህርቱ ተማሪዎች ወደ ግቢ ከመግባታቸው በፊት ለመጀመር በማኅበሩ የተመረጡና ልምድ ባላቸው መምህራን አማካኝነት ተዘጋጅተው የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች በየትምህርት ተቋማቱ እንዲሰጡ የማድረግ ሥራዎች እንዲሠራ አመራሩ ወሰነ፡፡

በውሳኔው መሠረት ሥልጠናውን ለመስጠት ተቋማት ውስጥ ሲኬድ ብዙዎቹ በሰንበት ትምህርት ቤት እየተማሩ ያሉ ጠንካራ መንፈሳውያን ወጣቶች እንዳሉ ሁሉ ይህን ዕድል ያላገኙ ብዙ ተማሪዎች በተለያዩ ኀጢ ሱሶች የተጠመዱ መሆናቸው እየተረጋገጠ መጣ፤ በመሆኑም ከዐሥራ ሁለተኛ ክፍል በፊት ያሉትን ተማሪዎች በሙሉ ተደራሽ ለማድረግ ትምህርቱ

እንዴት? በምን ያህል መጠን? ለምን ያህል ጊዜ? ለመሰጠት መሠራት እንዳለበት እና ኀላፊነቱን ወስዶ ሥራውን ሊያስተዳድረው ስለሚገባው አካል ለመወሰን ረጅም ጊዜ ወስዷል፡፡ ይህን ጉዳይ ለማስፈጸም የሚሆኑ ብዙ ጥናቶችም ተሠርተዋል፡፡

በመጨረሻም ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ጋር በጋራ ሥራውን መሥራት አገልግሎቱን ስለሚያቀላጥፈው እና ተደራሽነቱም ሰፊ መሆኑ ስለታመነበት አገልግሎቱን በጋራ ለመሥራት ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ኀብረት ጋር በመቀናጀት ለመሥራት የሚያስችል የትምህርት ሥርዓት (Syllabus) ተዘጋጀ፡፡

የትምህርት ሥርዓቱ ከአንደኛ ክፍል እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ መንፈሳዊ ትምህርትን የያዘ በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ ነው፡፡ የትምህርት ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ኀብረት ለቤተ ክህነት ቀርቦ ጸድቋል፡፡ በመቀጠል የትምህርት ሥርዓቱ (Syllabus) በየሰንበት ትምህርት ቤቶቹ ተግባራዊ እንዲደረግ ከሰንበት ትምህርት ቤቶቹ ጋር ውይይት ተደርጎ ተግባራዊ እንዲሆን ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የትምህርት ሥርዓቱ (Syllabus) ከተዘጋጀ በኋላ በሚፈለገው ልክ ተግባራዊ ተደርÕል?

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡-** ከተወሰኑት ሰንበት ትምህርት ቤቶች በስተቀር በሚፈለገው ልክ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ ከዚህ ላይ ተደራሽ እንዲደረግ ብዙ ሥራ መሥራት ይጠበቃል፡፡ ሥራውን በጋራ ለመሥራት ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ጋር ውይይት በተደረገበት ወቅት፤ ሰንበት ትምህርት ቤቶቹ ሥራውን ለመሥራት ፍላጎት ቢኖራቸውም የትምህርት ሥርዓቱ (Syllabus) ተግባራዊ ለማድረግ ግን ከማኅበሩ ብዙ እገዛን እንደሚፈልጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በወቅቱ ማኅበሩ ደግሞ በሚፈልገው ልክ ሰንበት ትምህርት ቤቶቹን ለመደገፍ የሚሆን በቂ አቅም አልነበረውም፡፡ በመሆኑም እንደገና የትምህርት ሥርዓቱን (Syllabus) እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ለማወቅ ብዙ ጥናቶች ተደረጉ፡፡ በጥናቶቹም መሠረት የትምህርት ሥርዓቱን (Syllabus) ተግባራዊ ለማድረግ የሚችሉ መምህራንን መረጃ እንዲያሰባስቡ እና እንዲያቀርቡ ዋናው ማእከል ማእከላትን እንዲመራ እና እንዲያግዝ፣ ማእከላት ወረዳ ማእከላትን እንዲመሩ እና እንዲያግዙ፣ ወረዳ ማእከላት አጥቢያዎችን እንዲመሩ እና

እንዲያግዙ፣ በሰንበት ትምህርት ቤት በኩልም ከቤተ ክህነት እና ከሰበካ ጉባኤ ጋር በየደረጃው ዝርዝር የሆነ የሥራ ድርሻ ተዘጋጅቶ ተሰጣቸው፤ ይህም ከበፊቱ በተሻለ ሥራውን ለመሥራት አግዟል።

ሥራው ሰንበት ትምህርት ቤቶች በዋነኝነት የሚያስተዳድሩት እንዲሆን ተደርጎ፤ ማኅበረ ቅዱሳን ደግሞ ባለው መዋቅር አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግበት እንዲሆን በመስማማት ከአንደኛ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርቱ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል ። ቅድመ ግቢ ጉባኤ ከላይ በተጠቀሰው አሠራር መሠረት ትምህርቱ እየተሰጠ መሆኑን እና አለመሆኑን በወረዳ ማእከላት እና በአጥቢያ ተወካዮች በኩል ይከታተላል ክፍተት በሚታይባቸው ቦታዎች ላይ ክፍተቱን ለመድፈን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ ያደርጋል።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የትምህርት ሥርዓቱ (Syllabus) መዘጋጀት አስፈላጊነቱ ምንድን ነው?

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡-** የትምህርት ሥርዓቱ (Syllabus) ትምህርቱን በቋሚነት ለማስተማር የተዘጋጀ ሰነድ ሲሆን እንደ መርጃ መሣሪያ ያገለግላል። ማኅበሩ በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ስለ ግሎባላይዜሽን እና ስለ ወቅታዊ ጉዳዮች ሰነዶችን እያዘጋጀ በየወቅቱ እንዲያቀርብም ስምምነት ስለነበረ ሰነዶቹ እየተዘጋጁ የአሠልጣኞች ሥልጠና ማሠልጠን ለሚችሉ ወንድሞች እየተዘጋጀ በመዋቅሩ መሠረት ለሚመለከታቸው የቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ተደራሽ እንዲሆንም እየተሠራ ይገኛል።

የቅድመ ግቢ ጉባኤ ትምህርትን በተመለከተ ከአንድ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ከተዘጋጀው የትምህርት ሥርዓቱ (Syllabus) በተጨማሪ ከዘጠኝ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሆኑ ዐሥራ አራት ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። እነሱም ለየሰንበት ትምህርት ቤቶቹ ተሰጥተው በሰንበት ትምህርት ቤቱ አስተባባሪነት በማኅበረ ቅዱሳን ደጋፊነት በሳምንት ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ለተማሪዎቹ በተዘጋጀ መርሐ ግብር እየተሰጡ ይገኛል።

ትምህርቶቹ መንፈሳዊ ትምህርትን እና የአስኳላውን ትምህርት እንዴት ማጥናት እንደሚገባ የሚያስረዱ የአጠናን ዘዴን የያዙ ትምህርቶችም ይገኙበታል። ይህም በተወሰኑ ቦታዎች ለምሳሌ ደሴ፣ ደብረ ብርሃን፣ ሐዋሳ፣ ድሬዳዋ፣ አዲስ አበባ እና ሌሎችም ቦታዎች ላይ በደንብ ተሠርቶበታል። ይህ አገልግሎት በተለይ ከገጠር ወደ ከተማ መጥተው፣ ቤት ተከራይተው፣

## ቅኝት

ከዘጠኝ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች፣ በቅድመ ግቢ ጉባኤ ውስጥ መማራቸው አላስፈላጊ ሱስ እና ተግባር ውስጥ እንዳይገቡ እንዲሁም በቀጣይ ግቢ ጉባኤን ለመማር ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ ረድቷል፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ለቅድመ ግቢ ጉባኤ ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው?

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡-** ወላጆች፣ መምህራን፣ ወረዳ ቤተ ክህነት፣ አጥቢያ ሰበካ ጉባኤ፣ ሰንበት ትምህርት ቤት፣ በተዋረድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ናቸው፡፡ ለምሳሌ መምህራን መደበኛ ትምህርታቸውን ያስተምሩዋቸዋል በተጨማሪም የቅድመ ግቢ ጉባኤ ትምህርትንም ያስተምሯቸዋል፡፡

የቅድመ ግቢ ጉባኤን ተግባራዊ ለማድረግ በወረዳ ቤተ ክህነት፣ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ኅብረት፣ በማኅበረ ቅዱሳን እና በወላጆች በኩል የትስስር ሰነድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ሰነዱ እያንዳንዱ ይህ አገልግሎት እንዲሳካ የሚሠራ አካል የሥራ ድርሻውን በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ በሰነዱ መሠረት መሥራት አሠራሩን ለማቀላጠፍ እጅጉን ይረዳል፡፡ ለምሳሌ በሰነዱ ውስጥ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን ከማገዝ አንጻር፤ በግቢ ጉባኤ የሚማሩ የተተኪ መምህራን ትምህርትን የሰለጠኑ ተማሪዎች፣ ቅድመ ግቢ ጉባኤ የሚማሩ ተማሪዎችን የሚያስተምሩበት አግባብ መኖር እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ ይህም ማለት የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች የተማሩትን መንፈሳዊ ትምህርት የማስተማር ሥራ ተግባራዊ ልምምድ የሚያደርጉት ቅድመ ግቢ ጉባኤ ውስጥ ነው፡፡ በተጨማሪም የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች የቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎችን የአስኳላ ትምህርት በማስጠናት ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ የማገዝ ሥራም ይሠራሉ፡፡ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች በተማሩት መንፈሳዊ እና የአስኳላ ትምህርት በሚያመጡት ለውጥ ደግሞ ወላጆቻቸው በመደሰታቸው ከበፊት ይልቅ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ከተጀመረ በኋላ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲልኩ አድርጓቸዋል፡፡

በሰነዱ መሠረት የሚኖሩ ወጪዎችን በአካባቢው ምእመናን እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው የሚማሩበትን ቦታ ከማመቻቸት ጀምሮ ለመምህራኑ የትራንስፖርት እስከመክፈል ድረስ የገንዘብ እና ሌሎችንም አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ለማሟላት የሚሠሩበት አግባብ እንደሚኖር ሰነዱ ያስቀምጣል፡፡

በትስስሩ መሠረት ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲልኩ፤ ልጆችም ረጅም ሰዓታቸውን በማይጠቅማቸው የቴክኖሎጂ

ውጤቶች ላይ በማሳለፍ አላስፈላጊ ወደ ሆነ ሱስ እንዳይገቡ ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ የሚሰጡ ሥልጠናዎች እንዲዘጋጁ ሰንበት ትምህርት ቤቱ ደግሞ እንዲያስተባብር ተደርÕል፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ቅድመ ግቢ ጉባኤ አገልግሎት በመቋቋሙ የመጣ ለውጥ ካለ ቢያስረዱን?

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡-** የመጣው ለውጥ ብዙ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ልከዋል፤ የቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ የሽኝት መርሐ ግብር ይዘጋጅላቸዋል፤ የማስታወሻ ሥጦታም ይሰጣቸዋል፤ ወደ ግቢ ጉባኤ ሲገቡም የቅድመ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች እንደነበሩ የሚገልጽ ፎርም ተዘጋጅቶ ይሰጣቸውና፤ ስለ ግቢ ጉባኤ አገልግሎት ገለጻ ስለሚሰጣቸው በቀላሉ የግቢ ጉባኤ አባላት ይሆናሉ፤ ሌሎችንም ወደ ግቢ ጉባኤ እንዲገቡ ለማድረግ ይሠራሉ፤ ግቢ ጉባኤዎችም በቶሎ እንዲቀበሏቸው የትስስር ሥራ ተሠርቷል፤ ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ረጅም ሰዓታቸውን በማይጠቅማቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ እንዳያሳልፉ የመገደብ ሥራ እየሠሩ ነው፤ ልጆቹም ሰዓታቸውን በመልካም ነገር የሚያሳልፉበት መንፈሳዊ እና አስኳላዊ እውቀት የሚገበዩበት ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ቅድመ ግቢ ጉባኤ እንዲጠናከር ምን ዓይነት ሥራዎች በቀጣይ መሠራት አለባቸው ብለው ያስባሉ?

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡-** ከዚህን በፊት እንደነበረው የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብሮች ለወላጆች ተጠናክረው መሰጠት ይኖርባቸዋል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኩ በተደጋጋሚ ሊሠራበት ይገባል፡፡ ይህም ወላጆች አገልግሎቱ እንዲጠናከር በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በሰንበት ትምህርት ቤት ደረጃም ሁሉም አገልግሎቱን እየፈጸሙ ስላልሆነ አንዱ ሰንበት ትምህርት ቤት ከሌላው ሰንበት ትምህርት ቤት የልምድ ልውውጥ እያደረገ አገልግሎቱ የሚሰፋበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የሽኝት እና የሽልማት መርሐ ግብሮቹ ቀጣዮቹን ተማሪዎች የሚያበረታቱ በመሆናቸው ትኩረት ተሰጥቷቸው መሠራት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ በዘንድሮ ዓመት በማኅበረ ቅዱሳን እና ሰንበት ትምህርት ቤቶች ኅብረት አስተባባሪነት ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት የተደረገው የሽኝት እና የሽልማት መርሐ ግብር ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡

የተደረገው የሽኝት እና የሽልማት መርሐ ግብር ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡

## ቅኝት







## ቅኝት

የቅድመ ግቢ ጉባኤ አገልግሎት የአጥቢያ አገልግሎት ነው በመሆኑም በማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ሲያገለግሉ የነበሩ አሁን ግን በትዳር፣ በወሊድ፣ በሥራ አለመመቻቸት፣ በትምህርት፣ በቦታ ርቀት እና በሌሎችም ምክንያቶች በማኅበሩ መዋቅር ውስጥ ማገልገል ያልቻሉ ወንድሞች እና እኅቶች በአጥቢያቸው ሆነው እንዲያገለግሉ የሚያስችል አገልግሎት በመሆኑ ስለአገልግሎቱ ለአባላቱም የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብሮች እየተዘጋጁ አገልግሎቱ አጥቢያቸው ድረስ መምጣቱን በመግለጽ አባላቱ በአገልግሎቱ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማመቻቸት ይገባል፡፡

አባላቱ በሰበካ ጉባኤ እና በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በመግባት እንዲሁም እንደ ወላጅ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማሟላት ለአገልግሎቱ መሳካት የድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል፡፡ ማገልገል እየፈለጉ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሳያገለግሉ ቆይተው ከረጅም ጊዜ በኋላም ለመመለስ የከበዳቸው አሁን እንዴት ብዬ እሔዳለሁ ለሚሉ አባላት በቀላሉ ሊያገለግሉበት የሚችሉበት እድል መሆኑን በማሳወቅ እና ለአገልግሎት አለመርፈዱን በማስረዳት ወንድሞቻችን እና እኅቶቻችንን ወደ አገልግሎት ለመመለስ የሚረዳን አማራጫችን ሊሆን ይችላል፡፡ ልጆችንም ከልጅነታቸው ጀምሮ ከመደበኛ ትምህርታቸው በተጓዳኝ የአብነት ትምህርትን እና የሰንበት ትምህርት ቤት ትምህርትን እያስተማርን ብናሳድጋቸው አጓጉል ለሆኑ ለወቅታዊ እና ለማይጠቅሙ በቴክኖሎጂ ሰበብ ከሚመጡ ክፉ ተጽእኖዎች ውስጥ ወጥተው መልካም ልጆች ሆነው እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል፡፡ ልጆቻችን ከቻልን በቤተክርስቲያን ካልቻልንም በየቤታችን የአብነት መምህራን እያስተማሩዋቸው እንዲያድጉ ብናደርግ፣ አፋቸውን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብለው እንዲፈቱ ብናደረጋቸው፣ በየቤታችን በየቀኑ የጸሎት መርሐ ግብር ቢኖር፣ የሰንበትን ቀን ሙሉ ቤተሰባችንን ይዘን ቅዳሴ ብናስቀድስ፣ በሰዓታቱ፣ በማኅሌቱ በንግሡም በቻልነው አቅም ብንሳተፍ፣ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለንን ትስስር የሚያጠናክሩልንን ክርስቲያናዊ ግዴታዎቻችንን ብንወጣ፣ ይህም ድርጊታችን ለጎረቤቶቻችንም ጥሩ ተሞክሮ ሆኖ ቢተገብሩት፣ እነዚህን አገልግሎቶች በኅብረት ሆነን ለመፈጸም ብንተጋገዝ፣ ከመጣብን መዓት ልንሰወርበት እንችላለን፡፡ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ተፈጠሩ ያልናቸውን ችግሮች ሊያጠፋልን ይችላል፡፡

መጽሔተ ተልእኮ፡- በመጨረሻም ስለ ቅድመ ግቢ ጉባኤ መነሳት አለባቸው የሚሏቸው ጉዳዮች ጠቅለል አድርገው ማንሳት ይችላሉ!

ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡- ለማጠቃለል ያክል ከሠራንበት ቅድመ ግቢ ጉባኤ



አገልግሎት ልጆቻችንን በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ለማሳደግ ጥሩ መሠረት የምንጥልበት የአገልግሎት መስመር ነውና በደንብ ተጠናክረን ልናገለግልበት የሚገባ የአገልግሎት ክፍል ነው። እያንዳንዳችን አርአያ የሚሆን ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ቢኖረን፤ ወደ ቀደመ መልካም ምግባራችን ብንመለስ በአገልግሎቱ ውስጥም እንደ ወላጅም፣ እንደ ልጅም እንደ መምህርም ሆነን የተጠናከረ ተሳትፎ ብናደርግ ቅድመ ግቢ ጉባኤ አገልግሎት መልካም ትውልድ የሚፈራበት የአገልግሎት ዘርፍ ይሆናል።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ጊዜዎትን ሠውተው ስለቅድመ ግቢ ጉባኤ አገልግሎት ክፍል ልምድዎትን ለማካፈል ፈቃደኛ ስለሆኑ በእግዚአብሔር ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ዓይናለም ታየ፡-** እግዚአብሔር ይስጥልኝ እኔም አመሰግናለሁ።

# “ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ” (ዕብ.፲፥፳፭)

ውድ የመጽሔተ ተልእኮ ተከታታዮቻችን! እንደምን ከረማችሁ? በዚህ ዓምድ ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን በያዝነው የአገልግሎት ዓመት በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች እያከናወናቸው ካሉ መንፈሳዊ ተግባራት ጥቂቶቹን እናስተዋውቃችኋለን፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ከተመሠረተበት ዘመን ጀምሮ በስብከተ ወንጌል፣ በግቢ ጉባኤያት፣ በገዳማት፣ በአብነት ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በተለያዩ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን እንደነበር ይታወቃል፡፡ አሁንም ይህን ታላቅ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግብሩን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን በዚሁ በያዝነው ዓመት ማለትም በ2015 ዓ.ም ከተገበራቸው ተግባራት መካከል ልናስቃኛችሁ ወደድን!

በአብነት ትምህርት ቤቶች፡-

አብነቱ ያለአብነት እንዳይቀር በማሰብ የቤተ ክርስቲያናችን የትምህርት፣ የዕውቀት፣ የፍልስፍና፣ እንዲሁም የክህነት ምንጭ የሆኑት አብነት ትምህርት ቤቶች በእጅጉ እየተዳከሙ፣ መምህራኑም ደቀ መዛሙርቱም እየፈለሱ እና ጉባኤ ቤቶቹም እየተዘጉ በመምጣታቸው በርካታ ችግሮች የተደቀኑበት መሆኑን የተረዳው ማኅበሩ በርካታ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ፣ መምህራኑና ደቀመዛሙርቱ እንዳይፈልሱ፣ ጉባኤው እንዳይታጠፍ፣ የነገዋ ቤተ ክርስቲያን በአገልጋይ እጥረት እንዳትዘጋ በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡ እያከናወነም ይገኛል፡፡

በዚህም በ2015 ዓም በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ብቻ ለ229 መምህራንና ለ1949 የአብነት ተማሪዎች በብር 2,872,200.00 ድጎማ ማድረጉ ለጉዳዩ የሰጠውን ትኩረት ያሳያል፡፡ ለአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነፃ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚዎች ከመንፈሳዊ ኮሌጅ 14፣ ከአብነት ወደ ዘመናዊ 15 እና ከዘመናዊ ወደ አብነት 57 በአጠቃላይ ለ46 የነፃ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚዎች በ1ኛ ሩብ ዓመት በብር 803,400.00 (ስምንት መቶ ሦስት ሺህ አራት መቶ ብር) ድጎማ ማድረግ መቻሉ ትልቅ ስኬት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ተግባር ነው፡፡

ከፕሮጀክቶቹ መካከል አንደኛው በሶማሌ ሀገረ ስብከት የተሠራው የደብረ ሰዋስው ቅድስት አርሴማ አብነት ትምህርት ቤት ግንባታ ፕሮጀክት እንዲሁም ሁለተኛው በከምባታ ጠምባሮ ሀላባ ሀገረ ስብከት ደብረ ፀሐይ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አብነት ትምህርት ቤት ግንባታ ፕሮጀክት ተጠቃሾች ናቸው። ሁለቱም ፕሮጀክቶች በየራሳቸው በየሁለት ዓመቱ 40 የአብነት ተማሪዎችን በመቀበል ከአብነት ትምህርቱ ጎን ለጎን መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት፣ የስብከት ዘዴና ልዩ ልዩ የዓቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎችን በመስጠት ዘመኑን የዋጁ የአብነት ተማሪዎች አስተምሮ ማብቃትን ዓላማ ያደረጉ ሲሆን የአብነት ትምህርት ቤት ግንባታቸው ተጠናቆ የተመረቁት በዚሁ ዓመት (በ2015 ዓ.ም ) ሲሆን በርካታ ነገሮችን ያካተቱ ናቸው። እያንዳዳቸው ግንባታዎቹ አርባ ደቀ መዛሙርትን በአንድ ጊዜ ማስተማር የሚችል አንድ ጉባኤ ቤት፣ ለሁለት መምህራን ቤት፣ አርባ ደቀ መዛሙርትን የሚያስተናግድ አምስት ክፍል ቤት በአንዱ ክፍል ስምንት ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችል አልጋ፣ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ፣ አንሶላ፣ ትራስ እና የዕቃ ማስቀመጫ ያላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ የመመገቢያ አዳራሽ፣ ዕቃ ቤት እና ለ40 ደቀ መዛሙርት መመገቢያ የሚሆኑ ጠረጴዛዎችና ወንበሮች ያሏቸው ሲሆን በተጨማሪም መጸዳጃና መታጠቢያ ቤት የተሟላላቸውና ዘመናዊና ምቹ ሆነው የተገነቡ ናቸው። በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ለማከናወን ማኅበሩ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሚኖሩ በጎ አድራጊ ምእመናንን በማስተባበር ግንባታ ሥራቸውን ብር 8,147,571.21/ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሰባት ሽህ አምስት መቶ ሰባ አንድ ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም /ወጭ አድርጎ ሠርቶ በማጠናቀቅ ኅዳር 10 እና 11 ቀን 2015 ዓ.ም አስመርቆ ለየሀገረ ስብከቶቹ ርክክብ አድርጓል።





ምስል1 . በሶማሌ ሀገረ ስብከት የተሠራው የደብረ ሰዋስው ቅድስት አርሴማ አብነት ትምህርት ቤት ግንባታ ፕሮጀክት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቡነ መቃሪዎስ ሲመረቅ

በአፋር ሀገረ ስብከትም በተመሳሳይ በማኅበሩ መጠነ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ሲሆን የዚህም ማሳያው የአዋሽ አርባ ደብረ ሐራ ቅዱስ ሚካኤል ወአቡነ አረጋዊ ገዳም የአብነት ትምህርት ቤት ታላቅ ፕሮጀክት ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በአካባቢው (በተለይም በአዋሽ አርባ በገጠራማ አካባቢዎች) የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በቂ ዲያቆናትንና ካህናትን እንዲያፈሩ፣ የተሟላ አገልግሎት የማይሰጥባቸው እንዲሁም የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲከፈቱ እና እንዲጠናከሩ በማድረግ ተገቢውን መንፈሳዊ አገልግሎት በማግኘት በሃይማኖታቸው ጽኑዓን የሆኑ ምእመናንን ማፍራት እንዲቻል ታስቦ እየተገነባ ያለ የአብነት ትምህርት ቤት ነው፡፡





ምስል 3 . በአፋር ሀገረ ስብከት አዋሽ አርባ ደብረ ሓራ ቅ/ሚካኤል ወአቡነ አረጋዊ ገዳም፤

ፕሮጀክቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ ሲሆን እስከ ኅዳር 30/2015 ዓ.ም ድረስ ብር 4,625,844.00 (አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አራት ብር ከዜሮ ሳንቲም) ወጪ ተደርጎበታል፡፡ የግንባታ ደረጃውም 83.58% የደረሰ ሲሆን በቅርቡ ተጠናቆ ወደ አገልግሎት እንደሚገባ ይታመናል፡፡

ሌላኛውና በዚህ ጽሑፍ ልናስተዋውቃችሁ የመረጥነው ከማኅበሩ ዐቢይ ተግባር መካከል በማእከላዊ ጎንደር ሀገረ ስብከት የደብረ መድኃኒት ዐቢየ እግዚእ ኪዳነ ምሕረት ወቅዱስ መርቆሬዎስ የመጻሕፍት ትርጓሜ ጉባኤ ቤትን የግንባታ ፕሮጀክት ነው፡፡ ዘመኑን የዋጀ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን በማፍራት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ዓላማ አድርጎ እየተሠራ ያለ ሲሆን በአብነት ትምህርት ቤቱ ያለውን የማደሪያ ቤት፣ የጉባኤ ቤት፣ የመጻሕፍት ቤት እና የሥልጠና ቦታ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ባለ 2 ወለል ሕንጻ በመገንባት ላይ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ግንባታ 37% የተከናወነ ሲሆን ለፕሮጀክቱም ትግበራ እስከ አሁን ብር 5,809,469.27 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ስድሳ ዘጠኝ ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) ወጪ ተደርጓል፡፡



ምስል 4 . በማዕ/ጎንደር ሀገረ ስብከት የደብረ መድኃኒት ዐብየ እግዚአ ኪዳነ ምሕረት ወቅ/መርቆሪዎስ የመጻሕፍት ትርጓሜ ጉባኤ ቤት ግንባታ ፕሮጀክት

ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን አርአያነት ያለው ግብረ ምንኩስና እንዲኖር የቅድስና ምንጭ የሆኑት ገዳማትም እንዲጠናከሩ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሆነም ይታወቃል፡፡ ለአብነትም በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በዋናው ማእከል እና በማኅበረ ቅዱሳን ጎንደር ማእከል ጋር በመተባበር 29,400.00 (ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ብር) ወጪ በማድረግ በማን እንደ አባ ገዳም አቡነ ያሳይ መድኃኔዓለም አንድነት ገዳም ለሚገኙ 28 መነኮሳት እና መነኮሳይያት ትምህርተ ምንኩስና፣ ኦርቶዶክሳዊ ሕይወት፣ ሉላዊነትና ዓለማዊነት፣ የአመራር ጥበብ፣ ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች እና የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን ይህ ተግባር በበርካታ ገዳማትም እየተከናወነ ይገኛል፡፡

የተወደዳችሁ የመጽሔታችን ተከታታዮች! ከላይ ያቀረብናቸው የማኅበረ ቅዱሳን የፕሮጀክት ተግባራት ከብዙዎች ውስጥ በጣም ጥቂቶቹና ለማሳያ ያክል የቀረቡ ናቸው፡፡ ገዳማትንና አብነት ትምህርት ቤቶችን ታሳቢ ያደረገ ሥራ መሥራት የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ማረጋገጥና የክህነት ተግባርን ማስቀጠል መሆኑን ከዚህ ጽሑፍ በመረዳት ማኅበረ ቅዱሳንን በሁለንተናዊ ዓቅም ማገዝ የዚህ ቅዱስ ተግባር ዓላማን መጋራት መሆኑን አውቀን የድርሻችን እንወጣ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

# ሰማዕትነት

በክርስናችን ጉዞ ውስጥ ከምንፈጽማቸው ጉዳዮች አንዱ የሰማዕትነትን መባእ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው። ሰማዕትነት የሥጋ ዕረፍት ነፍስ የምትሞሸርበት ስለ ሃይማኖት ጽናት የሚከፈል የክብር ዋጋ ነው።

በሐሙስ ውዳሴ ማርያም ‹‹ሰማዕታት የዚህችን ዓለም ጣዕም በእውነት ናቁ፤ ደማቸውንም ስለ እግዚአብሔር አፈሰሱ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሡ›› ይላል። ሰማዕትነት የዓለምን ጣዕም በመናቅ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ መንግሥት ጣዕመ ማዕድ ለመቅመስ የሚከፈል የሃይማኖት ፍሬ ነው፤ ተጋድሎውም ከሰው ጋር ያይደለ ከርኵሳን መናፍስት ጋር ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ ‹‹መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው›› በማለት እንደገለጸው ነው። (ኤፌ.፮፥፲፪) ለዚህም የሰማዕትነት ተጋድሎአቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በስማቸው ጽላት ቀርፃ፣ የሚከብሩበትን ዕለት ወስና እንዲታሰቡ ታደርጋለች። ይህም ለአምላካችን ታምነው ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ስለ ቅዱስ ቃሉ ሲሉ ዓለምን እንደ ውዳቂ ቆጥረው ራሳቸውን ለሰይፍ፣ ለእሳት፣ ለረኃብ፣ ለስደት እና ለእስራት ለብዙ መከራ ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠታቸው ነው። በዚህ ሁሉ መከራ ያለፉ እነዚህን የቤተ ክርስቲያን መብራት ሰማዕታት ሕይወታቸውን ዓይተን የራሳችንን ሕይወት መመልከት ያስፈልጋል። በዚህም ሂደት ውስጥ ሰማዕታቱን እናውቃቸዋለን? የሚል ጥያቄ ለራሳችን እናቅርብለት፣ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለን ተሰይመን በቤቱ እየተመላለስን ስለሰማዕታቱ ተጋድሎ እና ሕይወት የምናውቀው ዕውቀት እጅጉን አስፈላጊና መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

ዛሬ ዛሬ ለሰማዕትነት ወደ ኋላ እንድንል የሚያደርገን የሰማዕትነትን ክብር፣ የሰማዕታትን ሕይወት ጠንቅቀን ካለመረዳትም ጭምር ነውና ይህን ድክመታችንን ልንቀርፈው ያስፈልጋል። ሰማዕትነትን ስናስብ የምንዘክረው ስለክርስቶስ ሲሉ ደማቸውን ያፈሰሱትን፣ አንገታቸውን የተቆረጡትን፣ በመጋዝ ሰውነታቸውን የተሰነጠቁትን፣ የክርስቶስን ባለሚሎች ነው። በዚህም በሰይፍ የተቀሉትን እንደ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ፣ በመስቀል የተሰቀሉትን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያ፣ በአይሁድ በድንጋይ የተወገሩትን እንደ

## ሰማዕትነት

ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ በነገሥታት ፊት መስክረው የዓለምን ክብርና ሽልማት ንቀው ስለ ክርስቶስ መከራና ሥቃይ የተቀበሉትን እንደነ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ መርቆርዮስ፣ ቅዱስ መርምህናም፣ ክብርንና ዝናን እንደናቁት እንደ ቅድስት አርሴማ ያሉ እና በዘመናችንም ጠላት ሀገራችንን ሊገዛ ሃይማኖታችን ሊያጠፋ በመጣ ጊዜ ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰማዕት ወጻድቅ ዘኢትዮጵያ የተባሉት አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሚካኤል በአጠቃላይ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብለው መከራ መስቀልን የተቀበሉ የክርስቶስ አገልጋዮች የከፈሉትን ዋጋ ማሰባችንና መዘከራችን ነው፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም በክርስቶስ ደም ተመሥርታ በእነዚህ ሰማዕታት ደም የጸናች ተቋም ናት፡፡ ልንጓዝበት የተቀበልነው ክርስትና በብዙ ደም መፍሰስ፣ በብዙ ስደት፣ በብዙ ጭንቅና ሥቃይ፣ በብዙ ረኃብና ጥም እንዲሁም መከራ አባቶቻችንና እናቶቻችን እንዳቆዩልን በተረዳን እና ባሰብነው ቁጥር ዛሬ እኛ ልጆቻቸው ልንከፍል የሚገባውን ዋጋ በግላጭ ያሳየናል፡፡ ለዚህም የቅዱሳን ሰማዕታትን ታሪክ፣ ሕይወት፣ ተጋድሎና ጽናትም ጭምር ጠንቅቀን ማወቅና ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

ዛሬ በቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ እየተደረገ ያለው ቤተ ክርስቲያንን የማሳደድ ተግባር ታሪክ የሚዘክረው የቤተ ክርስቲያንን ውለታ የረሳ አሳዛኝና አሳፋሪ የዘመን ክስተት ነው፡፡ ለዚህም ተግባር እንደ አንድ ትውልድ የቤተ ክርስቲያናችንን ፈተና በልኩ በመረዳት ተጨማሪ ፈተናዋ ከመሆን ተቆጥበን ይልቁንም የሰማዕትነትን ሥራ የምንሠራበት ወቅት ነው፡፡ ‹‹መልካሙን ሥራችሁን ዓይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ›› ተብለናልና እስከ ሞት ድረስ ለመታመን ዝግጁ ሆነን በደም፣ በመከራ፣ በረኃብ፣ በሥቃይ የተረከብናትን ቅድስት ሃይማኖታችንን እኛም እንደ አባቶቻችን የመጣብን ፈተና በደምም፣ በመከራም፣ በስደትም፣ በርኀብም፣ በጥምም፣ በእስራትም ቢሆን ፈተናው የሚጠይቀውን ሁሉ ከፍለን፣ ለአምላካችን ታምነን፣ ሃይማኖታችንንና ታሪካችንን አስቀጥለን ለትውልድ ማስተላለፍ የእኛ ሃይማኖታዊ ግዴታችን መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡ (ማቴ.፭፥፲፮)

ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠውን መመሪያ በማክበር የአባቶቻችንን ቃል በማክበር ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅና በማስጠበቅ ዘመኑ የሚጠይቀውን የሰማዕትነት ዋጋ ልንከፍል ያስፈልጋል፡፡ ይህም ከስሜታዊነት በጸዳ መልኩ፣ ይልቁንም በማስተዋል፣ በጥበብ፣ በትሕትና እና በፍጹም መንፈሳዊነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ለመጠበቅ የሚጠበቅብን የአደራ መወጣት

ሂደት ነው፡ ለዚህም አፈጻጸም ቅዱስ ፓትርያርካችን አቡነ ማትያስ እንደ አስተላለፉት መልእክት "ሃይማኖታችን የደም ሥራችን" መሆኗን ተረድተን እስከመጨረሻው ልንጠብቃት ይገባል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በምክሩ ‹‹ተወዳጆች ሆይ! ስለ ሰማዕታቱ ብቻ የምትሰሙ አትሁኑ፤ እነርሱን ለመምሰልም ተጣጣሩ እንጂ ለጊዜው ብቻ የምታድነቋቸው አትሁኑ፤ ወደ ቤታችሁ ብቻ ሳይሆን ወደ ልቡናችሁ ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ አድርጉ፤ ዘወትር አስቧቸው፤ በልቡናችሁ ጓዳ እንዲገቡም አድርጓቸው፤ እናንተን ትተው ይሄዱ ዘንድ አትፍቀዱላቸው፤ ይህን ያደረጋችሁ እንደሆነ ዘወትር እያያችኋቸው ትበረታላችሁ፤ በእምነት ትጸናላችሁ፤ የለበሱትን የጽድቅ ጦር ያዙ፤ የያዙትን ምግባረ ወንጌል፣ የእምነት ጋሻ፣ የመዳን ራስ ቁር፣ የመንፈስ ቅዱስ ስም ሰይፍ እየተመለከታችሁ ትበረታላችሁ።›› ይህን ምክር በሕይወት እየተገበርን ከቅዱሳን ሰማዕታት ምልጃ ቃል ኪዳን እንድንጠቀም አምላከ ሰማዕታት ይርዳን፤ አሜን!

## ብሒለ አበው

- "አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"

  (ጠቢቡ ሰሎሞን)
- "በክርስቶስ ፊት ቆመህ በምትጸልይበት ጊዜ እንዳታፍር በሥራህ ሁሉ የሥጋን ንጽሕና ገንዘብ አድርግ።" (ማር ይስሐቅ)
- "ትግል፣ መከራና ፈተና ከሌለ የድል አክሊል፣ ጠባት ከሌለ ድል ማድረግ አይኖርም።" (ቅዱስ ባስልዮስ)
- "ልጄ ሆይ÷ አንተ በራስህ ላይ ስትፈርድ እግዚአብሔር ፍርዱን ያነሳልሃል፤ አንተ በራስህ ላይ ባትፈርድ ግን እግዚአብሔር ይፈርድብሃል።" (ታላቁ መቃርዮስ)
- "ወደ መኝታ ከማምራትህ በፊት የምታደርገውን ጸሎት ትተህ እንድትተኛ መንፈስ ሲገፋፋህ እሽ ብለህ አትቀበለው። እንዲያውም መዝሙረ ዳዊትን ጨምርና ሌሊቱን ሙሉ ስትጸልይ አደር።" (ማር ይስሐቅ)

# ናቡቴ ሆዩ ተነሠ!

በዱር በዋሻ ጤዛ  እየላሱ
ድንጋይ ተንተርሰው ጥሬ እየቀመሱ

መከራ መስቀሉን ከፊታቸው ስለው
ስላንቺ ተጥለው
እንደ መጻተኛ በሰው ዘንድ ተቆጥረው
ጺማቸው ተነጭቶ ቁልቁሊት ተሰቅለው
በሰይፍና በእሳት እጀግ ተፈትነው

ቆዳቸው ተገፎ
ጥርሳቸው ረግፎ

ዝንቱ ውእቱ ፍሬ ሃይማኖት
ብለው ያቀበሉን የሕይወት መልእክት

አርቀው በማየት ብራናውን ፍቀው
በደም የከተቡሽ ተዋሕዶ አንቺን ነው!

ቢያሽቱ ወደ አንቺ ጉባኤ ከለባት
ታሪክሽን ቢያጠፉ ግራኝና ጉዲት
ያደረሱት ጥፋት የታሪክ ጠባሳ
በልጆችሽ ልብ ውስጥ ቢልም አልረሳ
ማነው የጨከነ ቆርጦ የተነሣ
እንባሽን ሊያብስ ኀዘንሽን ሊያስረሳ

ብራናውን ዳምጠው
ቀለሙን በጥብጠው
ለእኛ ያቆዩልን ተጨንቀው ደጉሰው
ይህ ሁሉ ድካም ትውልዱ ካልገባው

በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱ

ምን ጥቅም ይሰጣል ...መባል! ለትውልዱ
እምነት ከምግባር በአንድ ካላስኬዱ

## አንተ ግን...

ቀና ቢሉ ላፍታ በደም የከተቧት
ስለ እርሱዋ መስክረው ያለፉት ሰማዕታት
አደራ የበላህ እጅግ አሳፋሪ
ሆነህ ሲያገኙህ ወጪቱን ሰባሪ

# ዋ!

ምን ትመልስ ይሆን ከፊታቸው ቆመህ
የአባቶችህን ርስት አደራውን በልተህ
ልጄ እባክህ አስተውል!
የወላድ መካን አትሁን፣ ደጇም አይዘጋ
ፍጠን አሁኑኑ አትሮንሱንም ዘርጋ
አንተ የናቡቴ ልጅ ክፈልላት ዋጋ

ናቡቴን አስበው ያ የተገፋውን ሰው
በኤልዛቤል ክፋት ደሙ የፈሰሰው
ለርስቱ ነበረ ሞትን የቀመሰው

መኖሪያቸው ሆኖ ዋሻ ሥር
ስለሱዋ ያነቡ ከልብ በፍቅር
ቅዱሳን ናቸው የእውነት ምስክር

ኃጢአት አይብቀል ብለው በቤቷ
እንዳይበላሽ ድንቅ ውበቷ

በቃ! መንጋው ከተኩላ ይለይ
እስከመቼ በቅጥርዋ ዝላይ!